**ኢትዮጵያ ።** **ITYOPPYA**

**“ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ ዕደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር” ።**

ግንቦት ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፳፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፤

<u>ተስፋ ፡ አስቆራጭም ፡ አንሁን!</u> <u>ከስለሺነህ ፡ ገላነህ ፤</u>

የሰው ፡ ልጅ ፡ መከራ ፡ አይድረስብኝ ፡ የማለት ፡ ብቃቱን ፡ የሚያስመሰክረው ፡ ከኃጢያተኛነት ፡ ሲርቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የሚያጋጥመውን ፡ ዕጣ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ “እግዚአብሔር ፡ ሰጠ ፣ እግዚአብሔር ፡ ነሣ ፣ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተመሠገነ ፡ ይሁን” ፡ ብሎ ፡ ጥናቱን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ ፈጣሪው ፡ አቤቱታን ፡ ማቅረብ ፡ ነው ። እከሌ ፡ እየበደለን ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ይልቅ ፡ እኛ ፡ ምን? እያደረግን ፡ ነው? መፍትሔው ፡ እኛ ፡ በኀብረት ፡ በመነሣት ፡ ስለሆነ ፡ ለኀብረቱ ፡ ዝግጁ ፡ ነን ፡ ወይ? ለውጭ ፡ ቅጥረኞች ፡ ከመካከላችን ፡ ሠርገው ፡ በመግባት ፡ ሲከፋፍሉን ፡ ለዕለት ፡ ጉርሳችን ፡ እንኳ ፡ በማይበቃ ፡ መደለል ፡ ተገቢ ፡ ነወይ?

ክቡራት ፡ እና ፡ ክቡራን ፡ ወገኖች ፡ ሆይ! ዛሬ ፡ እናንተን ፡ ለመማጸን ፡ የተነሣሣሁበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማዬ፦ የኢትዮጵያ ፡ አንበሣ ፡ (ኢትዮ ፡ ላዬን) ፡ ከሚመጣው ፡ ሐምሌ ፡ ፳፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጀምሮ ፡ እንደሚዘጋ ፡ “ማሳሰቢያ” ፡ አውጥቶ ፡ በማየቴ ፡ ነው ። ለመዘጋት ፡ ያደረሰውን ፡ ሁኔታ ፡ ጠይቆ ፡ እንረዳዳበት ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ እስተ ፡ አሁን ፡ ባለማግኘቴ ፡ እሰዬው ፡ ባዩ ፡ እንዳመዘነ ፡ ቆጥሬዋለሁ ። እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ፈጣሪ ፡ የሚያሰኝ ፡ እና ፡ ልሣናችን ፡ ሲዘጋ ፡ ዝምም ፡ ብለን ፡ ስናይ ፡ ጤናማነታችን ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀድም ፡ “በነፃ ፡ ኑሩ” ፣ “ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስተምህሮ ፡ ለኩሉ ፡ ዓለም” ፣ በተሰኙ ፡ ርዕሶች ፡ በመምህር ፡ ሐጎስ ፡ ዓለማዬሁ ፡ ጥሪ ፡ ተደርጎ ፡ የነበረውን ፡ ባለመገንዘባችን ፡ ይኸው ፡ አገራችን ፡ እየተቆረሰ ፡ ይሸጣል ። ሻጭ ፡ ወገኖቻችን ፡ የጥልያን ፡ እና ፡ እንግልጣር ፡ ጅምር ፡ ፈጻሚ ፡ ሆኑ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ “ተነሣ” ፣ “ፀፀት” ፣ ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ” ፣ (ሕዝቦች ፡ ለምን ፡ ያጉረመርማሉ) የቅንፉ ፡ ትርጉም ፡ የግሌ ፡ ስለሆነ ፡ ያጣሩ ። “በሃይማኖት ፡ ካባ ፡ የሚሠራ ፡ ደባ” ፣ በሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ለይኩን ፡ ብርሃኑ ፡ ሌላው ፡ ጥሪ ፡ ሲሆን ፡ በየገዳማቱ ፡ ያሉትን ፡ ጥንታውያን ፡ መጻሕፍት ፡ ባለግዜ ፡ መጤ ፡ ሃይማኖትን ፡ አልቃሽ ፡ ሰባኪዎች ፡ ለማቃጠል ፡ ፍለጋ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ተነቅቶባቸው ፡ እንደተቋረጡ ፡ አሳሳቢ ፡ ነበረ ። ቀሪዎችም ፡ ስለ ፡ ባሕሎቻችን ፡ እና ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎቻችን ፡ የሚያስተምሩንም ፡ ናቸው ። ለወደፊቱም ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ እንደሚኖርብን ፡ መክረውን ፡ ነበረ ። ባለመስማታችንም ፡ ይባሱኑ ፡ ገዳማት ፡ ተቃጠሉ ። ጥንታዊቷ ፡ ኢትዮጵያችን ፡ በ፲፰፻፹፰ ፡ ዘመን ፡ ዓይታው በማታውቀው ፡ ጥቃት ፡ በገንዛ ፡ ልጆቿ ፡ ተደፈረች ።

በተጨማሪም፦ “Ethiopia: THE CLASSIC CASE” ፣ “ኢትዮጵያዊው ፥ የማንነቱ ፡ ፍለጋ!” ፣ “ኢትዮጵያ ፡ የዓለሙ ፡ መፋረጃ” ፣ ኢትዮጵያ ፡ እና ፡ ኢትዮጵያዊነት” ፣ በተሰኙ ፡ መጻሕፍት ፡ የተከበሩ ፡ ንብረ ፡ ዕድ ፡ ኤርምያስ ፡ ከበደ ፡ ወልደ ፡ ኢየሱስ ፡ ጥሪያቸውን ፡ ያሰማሉ ። ጆሮ ፡ የእራሱን ፡ አይሰማም ። እና ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አይሰሜ ፡ ደንቆሮዎች ፡ መሆናችንን ፡ ሲያስገነዝቡንም ፡ “የሚደንቀኝ ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው” ። ያሉትን ፡ ማጤን ፡ ይገባል ።

እንግዲህ ፡ ወገኖች ፡ ሆይ! የኢትዮጵያ ፡ አንበሣ ፡ ሕዋ ፡ ሰሌዳ ፡ ልሣናችን ፡ መዘጋቴ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ሲያወጣ ፡ ዝምም ፡ ብለን ፡ ካሳለፍነው ፡ እኛም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገራችን ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖሩት ፡ ወገኖቻችን ፡ ሁኔታቸው ፡ ለዓለማት ፡ እንዳይሰማ ፡ እና ፡ እዚያው ፡ ታፍነው ፡ እንዲቀሩ ፡ እንፈልጋለን ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠን ፡ አስቆራጭ ፡ አንሁን ። ባይሆን ፡ የቁርጥ ፡ ቀን ፡ ልጆቿን ፡ ሕዋ ፡ ሰሌዳ ፡ እንዳይዘጋ ፡ እንረባረብ ።

በአምላኳ ፡ እርዳታ ፡ እና ፡ በቁርጥ ፡ ቀን ፡ ልጆቿ ፡ ብርታት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሸንፋለች ።